አፍሪካ ቲቪ

10

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት “የልብ ተግባራት” 3

በቴሌግራም

አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# ኹሹዕ (ትህትና)

**ኹሹዕ (ትህትና)፡- ኹሹዕ ማለት ማክበር ዝቅ ማለት መተናነስ የሚለውን ይተካል፡፡**

- ሁዘይፋ የንፍቅናን መተናነስ ተጠንቀቁ ሲሉ ይህ ማለት ምን ማለት ነው ብለው ጠየቋቸው እሳቸውም ሲመልሱ አካሉን ስትመለከቱ የፈራ የሚመስል ውስጡ ግን የማይፈራ ነው፡፡
- ሁዘይፋ በሌለ ጊዜም ለመጀመሪያ ከዲናችሁ የምታጡት ነገር ኹሹዕ ነው፡፡ ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ኹሹዕ የሚያስፈልገው የአምልኮ ተግባር ሁሉ ምንዳው በኹሹዑ ልክ ነው፡፡ ለምሳሌ ሶላት፡፡
- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሶላት የሚሰግድ ሰው (ከሶላቱ ግማሹን፣ አንድ/አራተኛውን፣ አንድ/አምስተኛው. … አስረኛውን እንጂ የለውም፡፡) ብለዋል፡፡
- ከቶዉንም ጭራሽ ኹሹዕ በማጣቱ ምንም የማይኖረው አለ፡፡

# አር-ረጃእ (ተስፈኘነት)

- **ተስፈኘነት ማለት :-** የአላህን ረህመት ስፋት መመልከት ነው፡፡
- ተቃራኒው ደግሞ ተስፋ መቁረጥ ነው፡፡
- በተስፈኘነት ላይ ሆኖ አምልኮ መስራት በስጋት ላይ ሁኖ ከመስራት እጅጉን ይበልጣል፡፡ ምክንያቱ በአላህ ላይ መልካም ጥርጣሬ ስለሚጨምር ነው፡፡
- አላህ ሱ.ወ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹እኔ ባርያዬ በጠረጠረብኝ ላይ ነኝ›› ብሏል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ተስፈኝነት ሁለት ደረጃ አለው፡፡
- ከፍተኛው አምልኮትን ሲተገብር የአላህን መልካም ምንዳ በመመኘት የሚተገብር ሲሆን እናታችን አኢሻ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ‹‹እነዚያም የሚሰጡትን ነገር ሁሉ እነርሱ ወደ ጌታቸው ተመላሾች መሆናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ሆነው የሚሰጡ ናቸው ›› ያለውን ቁርአናዊ ቃል እኒያ እየሰረቁ፤ እየዘሙቱ እና ኸምር እየጠጡ አላህን የሚፈሩ ሰዎች ማለት ነውን? አሏቸው፡፡ ነብዩም ﷺ አይደለም የሲዲቅ ልጅ ነገር ግን እኒያ እየሰገዱ እየፆሙ እየሰደቁ በዚህም ላይ አላህ አይቀበለንም ብለው ስጋት ያለባቸው ማለት ነው፡፡ ‹‹እነዚያ በመልካም ስራዎች ይጣደፋሉ፤ እነሱም ለርሷ ቀደሚዎች ናቸው፡፡›› ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ይህኛው ደግሞ ወንጀል ፈፅሞ ወደ አላህ ንስሀ ገብቶ የአላህን ምህረት የሚመኝ ነው
- ያ በወንጀል እንደተዘፈቀ የአላህን እዝነት ተስፋ የሚያደርግ ሰው ግን ከንቱ ምኞት ላይ ነው ያለው፡፡
- የመጀመሪያው የሚመሰገን ሲሆን ሁለተኛው ግን የተወገዘ ተግባር ነው፡፡
- ሙእሚን መልካም እየሰራ አላህን ይፈራል ሙናፊቅ ግን ክፉ ተግባር እየፈፀሙም ከምን ስጋትም የለውም፡፡

# ኸውፍ (አሏህን መፍራት)

- **ኸውፍ (መስጋት)፦** የሚጠላው ነገር እንዳይደርስበት የሚጨነቅ ሰው በስጋት ላይ ያለ ይባላል፡፡ እርግጠኛ ከሆነ ነገር ከሆነ ደግሞ ፍርሃት ይባላል፡፡
- ይህ ባህሪ የተስፈኝነት ባህሪ ተቃራኒ አይደለም እንዲያውም ይበልጥ በማነሳሳት ተስፈኝነት እንዲያጠናክር ይገፋፋል፡፡ ተስፈኝነት ደግሞ በመግባት በኩል ከፍተኛ አስተፅኦ አለው፡፡ እናም ሁለቱም በአንድ ሲገናኙ የተሟሉ ይሆናሉ፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- ኢብኑል ቀይም ልብ ወደ አላህ በሚያደርገው ጉዞ ልክ እንደ ወፍ ነው ይላሉ፡፡
- ውዴታ እንደ ጭንቅላት ስትሆን ስጋትና ተስፈኝነት ደግሞ ክንፎቹ ናቸው፡፡
- ስጋት በልብ ውስጥ ካለ በውስጡ ያሉትን ስሜቶች ያቃጥላቸዋል፡፡ የዱኒያ ፍቅርንም ያባርራል፡፡ ግዴታ የሆነው ስጋት ግዴታን ለመስራትና የተከለከሉ ነገሮችን ለመተው የሚያስችል ያህ ነው፡፡ የሚወደደው ስጋት ደግሞ የሚወደዱ ነገሮችን ለመተግበርና የተጠሉ ነገሮችን ለመተው የሚያስችል ያህሉ ነው፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

- ስጋት ብዙ ክፍሎች አሉት፡፡

**1)** ውስጣዊና አምልኮ ስጋት አለ እሱም ለአንድ አላህ ብቻ መሆን አለበት፡፡ ይህ አይነቱን ስጋት ከአላህ ሌላ ለሆነ ለምሳሌ ለአማልክቶች የሚያደርጉትን መንፈሳዊ ፍርሃትን ይመስል ከፍተኛ ሺርክ ነው፡፡

**2)** የተከለከለው ስጋት ሲሆን ይኸውም ሰዎችን ፈርቶ አላህ ያዘዘውን መተው ወይም የከለከለውን መስራት ነው፡፡

**3)** የተፈቀደ ስጋት ሲሆን እሱም በተፈጥሮ የሚያስፈራን ነገር ለምሳሌ አንበሳ፤ ነብር፤ ተኩላ እና ውሻ መፍራት ይመስል ነው፡፡